የሰ/መ/ቁ 88542

ሐምሌ 17 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ቢሆነኝ ደምሌ - ጉዳይ ተከታታይ መንበሩ ተስፋው - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የት/ብ/ክ/መንግስት ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ንግድ ፈቃድ ሳይኖረው የንግድ ሥራን በህገ ወጥ መንገድ ማከናወን ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው በት/ብ/ክ/መንግስት አላማጣ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ አመልካች ላይ ባቀረበው የወንጀል ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካች ንግድ ፈቃድ ሳይኖረው በ17/11/2004 ዓ.ም ከጥዋቱ 3:00 ሰዓት አካባቢ በአላማጣ ከተማ 02 ቀበሌ ልዩ ቦታው ወደ ዋጃ መውጫ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ አንድ ኩንታል ስኳር በመኪና ላይ ጭኖ ወደ ቆቦ ወረዳ ሲጓዝ ስለተያዘ አዋጅ ቁ 686/2002 አንቀፅ 60/1/ ተላልፎ በፈፀመው ሕጋዊ ያልሆነ ንግድ ሥራ በማካሄድ ተከሷል የሚል ሲሆን ተከሳሹም ቀርቦ ስኳሩን ወደ ቆቦ ከተማ ወስዶ ለመሸጥ በመኪና እየተጓዘ ሳለ መያዙን ጠቅሶ ንግድ ፈቃድ ሳይኖረው ይሄንን የንግድ ሥራ መፈፀሙ ጥፋት መሆኑን በማመን የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው ወረዳ ፍ/ቤትም ተከሳሹ የሰጠውን የእምነት ክህደት መነሻ በማድረግ ተከሳሹን በተከሰሰበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ካደረገ በኃላ በሁለት ዓመት ፅኑ እስራትና ብር 150,000 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺ.ህ) ገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወሙ ቅሬታውን ለዞኑ ከፍ/ፍ/ቤትና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃውን ጠብቆ ቢያቀርብም በሁለቱም ደረጃ ተቀባይነት አላገኘም አሁን የቀረበው የሰበር

አቤቱታም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም አንዱን ኩንታል ስኳር ገዝቼ ወደ ቆቦ ከተማ ስንጓዝ የነበረው ለንግድ ወይም ለሽያጭ ሳይሆን ወላጅ አባቴና ሴት አያቴ በሞት በመለየታቸው ምክንያት ለሃዘን ለሚመጡ ሰዎች ሻይና ቡና ማስተናገጃ ሆኖ ሳለ ጥፋተኛ መባሌ አላግባብ መሆኑን ለንግድ ነው ቢባል እንኳ የቀረበብኝን ክስ ሙሉ በሙሉ በማመን የእምነት ክህደት ቃልን መስጠቴ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኔን የወንጀል ሪከርድ የሌለብኝ መሆኔ የግል ሁኔታዬና የገቢ ምንጭ በወንጀል ህግ ቁ 88/2/፤ 90/2/ እና እንዲሁም በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በአግባቡ ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ ቅጣቱ መጣል ሲገባ ያላግባብ በሁለት ዓመት ፀኑ እስራትና 150,000 ብር የገንዘብ መቀጮ እንድቀጣ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ውሳኔው ተሻሽሎ የጥፋተኝነት ደረጃዬን ባገናዘበና የገንዘብ መቀጮውንም በተመለከተ የመክፈል አቅሜን ባገናዘበ መልኩ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

አቤቱታውም ተመርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል መባሉ ተጠሪም ቀርቦ የበኩሉን መልስ የሰጠበት ሲሆን አመልካችም የመልስ መልሱን ሰጥቶበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር አቤቱታ በቀረበበት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል::

እንደመረመርነውም የጥፋተኝነት ውሳኔን በተመለከተ አመልካቹ የቀረበበትን የወንጀል ክስ መፈፀሙን በዝርዝርና ሙሉ በሙሉ በማመን የእምነት ክደት ቃሉን መስጠቱና ፍ/ቤቱም ይህንኑ የአመልካችን የእምነት ቃል መነሻ በማድረግ የጥፋተኝነት ውሣኔ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.134 /1/ ድንጋጌ አንፃር መስጠቱን መገንዘብ ተችሏል ሆኖም ግን አንድ ሰው በተሰጠበት የጥፋተኝነት የቅጣት ውሳኔ ላይ ደረጃውን ጠብቆ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ይግባኝ ለማለት የሚችል ቢሆንም የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠው በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ134/1/ ስር እንደተመለከተው የተከሳሹን የእምነት ቃል መነሻ በማድረግ ከሆነ በቅጣቱ ላይ ካልሆነ በጥፋተኝነቱ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ እንደማይቻል በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 185/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም በአንድ በኩል አመልካች ወንጀሉን በህጉ አግባብ ሙሉ በሙሉ መፈፀሙን አምኖ የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቶና የጥፋተኝነት ውሳኔም ይህንኑ መነሻ በማድርግ ተሰጥቶ እያለ በሌላ በኩል ደግሞ በበታች ፍ/ቤት ከሰጠው እምነት ቃል በተቃራኒ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ እርስ በራሱ የሚጋጭ በመሆኑ ተቀባይት ያለው አይደለም ብለናል፡፡

የቅጣት ውሳኔን በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የህጉ ድንጋጌ ከብር 150,000-300,000 የገንዘብ መቀጮና እንዲሁም ከ7-15 ዓመት ፅኑ እስራት እንደሚያስቀጣ የደነገገ ሲሆን

ከዚህ አኳያ የእስራት ቅጣቱን በተመለከተ የበታች ፍ/ቤቶች የወንጀሉን ክብደት የአመልካቹን የግል ሁኔታና ሌሎች የቅጣት ማቅለያዎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በድንጋጌው ስር ከተመለከተው መነሻ የእስራት ቅጣት (7 ዓመት ፅኑ እስራት) በመውረድ አመልካቹ በሁለት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ የተወሰነበት ሲሆን ይህ ደግሞ ሊነቀፍ የሚችልበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታም አልተቀበልነውም፡፡

በሌላ በኩል የገንዘብ መቀጮውን በተመለከተ  በወ/ህ/ቁ 90/2/ ስር እንደተመለከተው ፍ/ቤቶች ይህንን የገንዘብ መቀጮ ሲወስኑ የወንጀሉ ክብደት የአጥፊውን  አደገኛነት መጠን የሀብቱን ሁኔታ የገቢ ምንጩን ዕድሜውንና የጤንነቱን  ሁኔታ ከቤተሰብ አስተዳዳሪነት አኳያ ያለንበትን ሸክም  የሙያ ስራውንና ከስራው የሚያገኘውን ገቢ መጠን ከግምትና ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ ሁኔታ መቀጮው ሊጣል እንደሚገባ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ይሁን  እንጂ በተያዘው ጉዳይ በአመልካች ላይ የተጣለው የብር 150,000 የገንዘብ  መቀጮ  እነዚህ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን የህጉን መስፈርቶች ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ አግባብ መሆን አለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ አያሳይም የመቀጮ ቅጣቱ እነዚህ መስፈርቶችን ባላገናዘበ ሁኔታ የሚጣል ሆኖ ከተገኘም የወንጀል ህጉ  ካሰበው ዓላማ ውጭም በመውጣት አጥፊውንና ሌሎቹን ከማስተማር እና ከማስጠንቀቅ አልፎ አላስፈላጊ ጫናና ችግር በተከሳሹና  በቤተሰቡ ላይ እንዳይፈጥር ጭምር ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል በተለይም አመልካቹ አርሶ አደርና የቤተሰብ አስተዳዳሪ  ከመሆኑ አኳያ የሀብቱ ሁኔታ የገቢ ምንጩ  አደገኛነቱና የወንጀሉ ክብደትም በተገቢ ሁኔታ ተመዝኖ መታየት ከነበረበት ባጠቃላይ በህጉ እስካልተከለከለ ድረስ በህጉ ከተመለከተው መነሻ መቀጮውም በመውረድ (አጠቃላይ የገንዘብ መቀጮው መነሻ እንደተጠበቀ ሆኖ) መቀጮው በወንጀል ህጉ አግባብና በተለይም በወ/ህ/ቁ88/2/ ፤ 90/2/ እና በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በወጣው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ 1/2002 አኳያ መጣል ሲገባ በደፈናው አመልካቹ በብር 150,000 እንዲቀጣ መወሰኑና ይኼውም  በዞኑ ከፍ/ፍ/ቤት እና ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መታረም ሲገባ መፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፤

## ው ሳ ኔ

1. በአላማጣ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት መ.ቁ 03421 በ15/2/2005 ዓ.ም ተወስኖ በከፍተኛ ፍ/ቤቱና ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የፀናው የጥፋተኝነትና የእስራት ቅጣቱ ውሳኔ ክፍል በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ.195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት ፀንቷል፤
2. ሆኖም ግን አመልካች በብር 150,000 (መቶ ሃምሳ ሺ.ህ) ገንዘብ መቀጮ ይቀጣ በማለት የተሰጠው የቅጣቱ ውሳኔ  ክፍል ብቻ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 195/2/ /ለ/ /2/ መሰረት ተሽሯል፤

3. የአላማጣ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የራሱን መዝገብ በማንቀሳቀስና ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኂላ ከዚህ በላይ በፍርዱ ሐተታ ክፍል በተገለፀው አኳኋን የገንዘብ መቀጮውን ከወንጀል ህጉ ቁ 90/2/፤ 88 /2/ እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካላቸው ሌሎች  ድንጋጌዎችና እንዲሁም በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በወጣው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ 1/2002 አኳያ የገንዘብ ቅጣቱን በማገናዘብ ከመረመረ በኃላ ተገቢውን አስልቶ እንዲወስን ዘንድ ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፤

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ